ኦሕንኢአ

OPMEU

opmethio12@gmail.com

# የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት

## ኦ.ሕ.ን.ኢ.ኣ

በየኦሮሞ ሕዝብ ለኢትዮጵያ እንድነትና ሕሊዉና እስከዛረ የከፈለዉ መስዋእት እጅግ በጣም_ብዙ ነው፥ አባቶቻችን ከቅርብ ተስፋፊዎችና ከሩቅ ወራሪዎች የተፋለሙትንና ገድላቸውን በዝርዝር ለመግለጽ ይከብዳል ፣ አባቶቻችን ኢትዮጵያ በጠላት እንዳትወረር የሕይወት መስዋዕት ሲከፍሉ እንደኖሩ ታሪካቸው በአያለው ያስረዳናል፥ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን አገራችንን ከሩቅ ወራሪዎች ተከላክለ ያኖ ሩዋት በተናተጠል ሳይሆን ከለሎችም ብሐር ብሐረሰቦች ጋራ በመተባበር እንደሆነ ታሪከ ማስረጃ ጠቅሶ ይነግረናል።

አባቶቻችን ሀገራችን ኢትዮጵያን በግንባር ቀደም ተከላክለዉ ያኖሩዋት በመተባበራቸዉና በመግባባታቸዉ ነዉ፣ጠላት ከጠረፍ ታየ የሚል ጥሪ ሲደርሳቸው ቤቴን ፣ንብረተን፣ሚስቴን ሣይሉ የእርስሻ መሳሪያቸዉን ከዛፍ ሰቅለዉ ያለቻዉን የመከላከያ ኋላ ቀር መሣሪያ ከወገባቸው ሸጥ አድርገው ጠላትን ሲገጥሙ የተሳካላቸው ጠላትን ከአፈር ደባልቀው በድል ሲመለሱ ያልተሳካለቸው ደግሞ ጠላትን አደባይተው ከጠረፉ ሲቀሩ ኖረዋል፣በኛም ዕድመ ተከስቶ የተወጣነው እጅግ በጣም ብዙ ታይተዋል፣ እብርተኞች ሲመጡብን አንሸበርም፣አንጨነቅምም ፣ ለዚህ ነዉ ጠላቶቻችን ገፍትው ሲመጡ ***እናንተ ከአባቶቻችሁ አትበልጡም እኛም ከአባቶቻችን አናንስም ስለሆነም ከዉጊያው ሚዳ እንገናኝ*** ብለው ወደ ግንባሩ የሚተሙት፣ለዚህ የምንሰጠው ሐረግ "ጥለው የወደቁት የድንበር አጥር ሆነዉ ይኖራሉ= ብለን ለዘላለም የሚ ንመካባቸውና የምንኮራባቸው፣

የኢትዮጵያ ብሐር ብሐረሰቦች የየራሳቸዉ የመኖራቸዉ ክልል እንዳላቸው ለማንም ግልጽ ነዉ፣ሁሉም የየራሳቸዉ መኖርያ ክልል ቢኖራቸዉም በአስፈለጋቸዉ ቦታ የመኖር መብት እንዳላቸዉ ደግሞ ማንም የሚያዉቀዉ ነዉ፣ ስለሆነም መላ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች አንዱ ከለላዉ ተዋልደዉ ኑሮቸዉን ሲመሩ ይስተወላል። የደም ግንኙነቱና ትስስሩ በጣም የሰፉ መሆኑን ማንም የሚያውቀውነው፤

ወያነ ሥልጣን ከተቆናጠጠ በኋላ ግን የወያነ አቀንቃኝ ሆነው የተነሱ ጥቂት የኦሮሞ ምሁራን ወያነ በከፈተላቸዉ ቀዳዳ በመውጠቀም የኦሮም ሕዝብ በኢትዮጵያ በሃገሩ ውስጥ ተጨቛኝ እና ተበዝባዥ እንደሆነ በመለፈፋቸዉ ይህ ሰፊ ሕዝብ ሆድ እየባሰው ሃደ።እስከ ወያነ ስረእት ድረስ በኢትዮጵያ ብሀር ብሀረሰቦች ሳይከፋፈሉና ሳይለያዩ አብረዉ ኖረዋል፣ወያነ ሥልጣን ከተቆናጠጠ በኋል የኦሮሞ ብሐር ብቻ ሣይሆን የአገሪቱ ብሐር ብሐረሰቦች ሰላም አጥተው መታመስ ጀመሩ፤ ብልጣ ብልጡ ወያነ ከፊሉ የኦሮሞን ሊቃን በጥቅም በመያዝ እርስ በርስ እያናቆረ፣አብሮ ከኖረዉ ሕዝብም ጋር እያናከሰዉ ወያነና ግብረ አበሮቹ ኦሮሞን እየገደለና በየእሥር በቱ እያሰቃየ የኦሮሞን ጥሪት እያጋዘ በባእዳን አገር እያከማቹ ኑሮውን አበጃጅተዋል ፤ የኦሮሞ ሕዝብ ዛረ የተጋረጠበትን የወያነ የጉሮሮ አጥንት ጎልጉሎ ከማዉጣት ይልቅ

አብሮ ከኖረው ብሐር ብሐረሰቦች ጋር እይተጨፋጨፈ ሲገኝ «ተው አይገባም>. ብሎ ከመሃል ገብቶ አስማምቶ ጸረ ወያነ ትግል የሚያበረታታ አካል አልተገኘም። ግፉ እየበዛ፥ መከራው እየሰፋ ሲሄድ ባዶ እጁን ትግል ጀመረ፣ የባዶ እጅ ትግል  የኦሮም ወጣቶችን ከመጉዳት በቀር እስከ አፍንጫዉ የታጠቀውን ወያነን ለማጥቃት እንደማይችል ከወዲሁ መገመት አልከበደም። በእልህ የተነሣውን ወጣት እና <‹ለጅ ከተቀጠፈ እነስ ምን ቀረኝ>› ብሎ የተነሣውን ወላጅ መሥመር አስይዞ የሚያንቀሳቅስ አካል ባለመገኘቱ አያለው ጉዳት በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ደረሰ፣

ኅብረት ማጣትና ከለሎቹ ብሐር ብሐርሰቦች ጋር ቅንጅት አለመፍጠር ዛረ ወያነ የኦሮሞን ሕዝብ ከፉኛ  እንድበድል ጥሩ አጋጣሚ ፈትሮለታል፣ ለዚህ ደግሞ ያበቃው አንዳንድ ጥቂት የኦሮሞ ሕዝብ ምሁራን ኦሮሞ ከለሎቹ ኢትዮጵያውያን  ወገኖቹ ጋር እንዳይስማማ  ሰንካላ ምክንያቶች  በመፍጠራቸው ነው፤ በአሁኑ ወቅት አንዳንድ የተለያዩ ኢትዮጵያዊ ብሐረሰቦች እርስ በርስ እየተጋጬ ናቸው፥ ይህ ደግሞ ለወያኔ ሥርግና ምላሽ ነው፣ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ከሁሉም የከፋ የኦሮሞ ሕዝብ ህሊውና ከአጠያያቂ ደረጃ ላይ እንደሚወድቅ ጥርጥር የለዉም፥

አደጋው እያንዣበበው ነው፥ ይህን የሕሊውና ጥያቀ ዛረ መመለስ ያለበት የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው ኢትዮጵያን ወዳድ ዘጎች ጭምር ነው፥ የኦሮሞ ሕዝብ ከለላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እንዳይተባበር ወያነ ቀን ተለት ተግቶ እየሠራ ነው፣የወያነን ሚስጥራዊ ደባ ማምከን የሚቻለው የኦሮሞ ሕዝብ ከለሎች ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ሕብረት ሲፈጥር ብቻ ነው፣ የጉዳዩን አሳሳቢነት በሰፊው በመመልከት በርካታ የኦሮሞ ምሁራን ተሰብስበው፤ የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቀ ለኢትዮጵያ አንድነት «አ ሕ ን ኢ አ »የሚባል የፖለቲካ ድርጅት እንዲመሠረት ተስማምተዋል፣ይህ የፖለቲካ ድርጅት በኦሮሞ ታሪክ ውስጥ ከለሎች የኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ሲተባበር የመጀምውሪያ የፖለቲካ ድርጅት ሲሆን ዋና መሰረተ ዓላማው  በጋራ በመተባበር የኦሮሞን ሕዝብና የለሎችንም ሕሊውና ለማስጠበቅ ታስቦበት የተመሰረተ  የፖለቲካ ድርጅት ነው፣

| | |
|---|---|
| ክፍል አንድ | ፖለቲካዊ መርሆ |
| ክፍል ሁለት | የምጣነ ሐብት መርሆ |
| ክፍል ሶስት | የመከላከያ መርሆ |
| ክፍል አራት | ማህበራዊ ግንባታ መርሆ ናቸው |

## ክፍል አንድ

### ፖለትካዊ  መርሆ

- .ዓርማው የኢትዮጵያ የዘላዓለም የነፃነት ምልክት የሆነች አረንጓደ ብጫ ቀይ ባንዲራችንና የቡና ተክል ነው፤ የቡና ተክል የመረጥነው ከታሪካችንና ከምጣነ ሐብታችን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው.
- ኦሕን ኢ አ የራሱ የሆነ ብቸኛ ዋና ከተማ እንዲኖረው ባይሻም ከለሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመመካከር ከታሪክና ከረጅም እዉቅና ጋር በተያያዘ ሁኔታ ላይ በመመርርኮዝ ይወሰናል፤
- ኦ ሕ ን ኢ አ የሥራ ቋንቋ አማርኛ እና የኦሮምኛ ቋንቋን ስንመርጥ ለሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች በምርጫው ላይ የየራሳቸውን ማኅበረሰብ ወክለው እንደሚጋበዙና ሃሳብ እንደሚሰጡ ያረጋግጣል፣
- የኦሮሞ ሕዝብ ወያነ ከተገረሰሰ በኋላ ከክልላዊ አመለካከትና ከጎጠኝነት ትሥሥር እንዲሁም ከአምባገነናዊ አገዛዝ ነጻ የሆነ ደሞክራሲያዊ መንግሥት ተመስርቶ ሕዝባችን በሰላምና በብልጽግና እንዲኖር የሚያስችለውን የሕግ ልዕልና ባላቸው ባለሦስት አምድ ማለትም በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈጻሚው እና በፍትህ ሰጪ አካሎች ተካፍሎና መሠረተ ዓላማው የሕዝብ፣ ለሕዝብ ፣ ከሕዝብ ሆኖ ሕዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ እንዲከበርና እንዲረጋገጥ ኦሕንኢአ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፣

❖ ማንኛውም በኦሮሞ መሬት ላይ የሚኖር እንዲሁም የተወለደ እድሜው ሃያ ዓመት የሞላው ለሁለት ዓመት ብሐራዊ አገልግሎት የማበርከት ግዴታ እንዳለበትና ከሃያ አምስት ዓመት በላይ የሆነ እንደማይገደድ ኦ ሕ ን ኢ አ ያምናል፣

❖ ኦሕን ኢአ የማንኛውም ሰው ሰብ አዊ መብቱ መከበር እንዳለበት ሲገልጽ ማንም ሰው በሕግ ፊት እኩል መሆኑን ያረጋግጣል፣

❖ ኦ ሕ ን ኢ አ ከኦሮሞ ሕዝብ ጎን መላው የኢትዮጵያ መብት ለማስከበር በመላው የአገሪቱ ክልሎች ጽሕፈት ቤት ከፍቶ አባሎቹን ለማደራጀት አቅዶአል።

❖ ኦ ሕ ን ኢ አ ከተናጠል እስከ ብዙኃን ነጻነት ቢያምንም በአገር መገንጠልና በሕዝቦች መለያየት ላይ ፍጹም አይደራደርም፣ በምትኩ በሕዝቦች መካከል ድንገተኛ አለመግባባት ቢከሰት እንኳን ለችግሮቹ መፍትሀ ማምጣት የሚቻለው በውይይት መሆኑን ያምናል፣ በአንጻራዊ መልኩ ደግሞ አምባገነንነትንና ትዕብተኝነትን ያወግዛል፣

❖ ከሞላ የኢትዮጵያ መሬት በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩ በኦሮሞ መሬት መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በዴሞክራሲያዊ ድምጽ አሰጣጥ ሁሉም እኩል መሆናቸውን ኦሕን ኢአ በጽኑ ያምናል

❖ ኦ ሕ ን ኢ አ የአገር አንድነትን የማይጻረሩና የሕዝባችንን ጥቅም የሚይጋፉ የፖለቲካ ወይም ሰብ አዊ ድርጅቶች ቢፈጠሩ አይቃወምም፣ ድጋፍም ይሰጣቸዋል፣

❖ ቅድሚያ ለውጭ አገር ዜጋ የሚለው ዘመኑ ያለፈበት የተለምዶ አባባል ቀርቶ ቅድሚያ ለዜጎቻችን መሰጠት እንዳለበት ኦሕ ን ኢ አ በጽኑ ያምናል፣

❖ አንድ የውጭ አገር ዜጋ በራሱ ስም መሬት መግዛት ወይም ሕንጻ መገንባት እንደማይፈቀድለት ቢያምንም መንግሥት ወይም የአገሪቱ ምክር በት ከወሰነ ግንተቃውሞ የለዉም፣

❖ ኦ ሕ ን ኢ አ በኢትዮጵያ አንድነት ስለሚያምን የራሱ የሆነ የውጭ ጉዳይ ተጠሪ ባይኖረውም የራሱ የቃል አቀባይ ይኖረዋል፣

❖ ሕዝባችን ራሱን ለመከላከል በማዕከላዊ መንግሥት የሚታወቅ ነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያ የመያዝ መብት እንዳለው ኦ ሕ ን ኢ አ ያምናል፣ ይህ መላው ሕዝብ በጅምላ የጦር መሣሪያ ይታጠቅ ማለት ሣይሆን የዕድመ ብቃትና የአዕምሮ የጠንነት መለኪያ ተገግሞ መሆን የሚኖርበት ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል፣

❖ ወንጀል ነክ ወይም ፍትሐብሔር ጠቀስ ክሶችን በተመለከተ ከመንግሥት መመሪያ ጋር ይስማማል፣ የፍትህ አሠጣጥን በተመለከተ ሚስጥርዊ ክትትል ያደርጋል

❖ በአርሦ አደር እና በአርብቶ አደር ሕዝባችን መካከል የሚታየው መግባባት ተጠናክሮ መቀጥል እንዳለበት ኦ ሕ ን ኢ አ ያበረታታል፣

❖ በአርብቶ አደሮች በግጦሽ መሬት ላይ መጋጨትና መጣላት እንዳይኖር ሁሉም ተባብረው እንዲጠቀሙ ከሁሉም በተውጣጣ ሽማግለዎች እንዲተዳደሩ ኦ ሕ ን ኢ አ ያበረታታል፤

❖ ዜጎችን ከአገር ወደ ለላ አገር በሚያሸጋግሩት ላይ መንግሥት አስፈላጊ እርምጃ ይወስድ ዘንድ ኦ ሕ ን ኢ አ በጽኑ ያምናል. እንዲሁም አንድ የአገሪቱ ዜጋ አገር ጥሎ ያለምንግሥት ፍቃድ ከአገር ከወጣ ወይም ካኮበለለ በአገር ክህደት ወንጀል እንዲጠየቅ ኦሕ ን ኢአ ያምናል፣

❖ ኦ ሕ ን ኢ አ በኢትዮጵያ አንድነት ስለሚያምን የኢትዮጵያ የባህር በርም ሆነ በወያነ የተዛቡ የጠረፍ ግዛቶች ከታሪክ አኳያ በተገናዘበ መልኩ መስተካከል እንዳለባቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ያሳስባል፣ የኢትዮጵያ በር በዓለም አቀፍ ሕግ እንዲመለስላትና ኢትዮጲያ የባሕር ኃይሉዋን መልሳ መገንባት እንዳለባት ሲያምን ለዚህ እንቅፋት የሚሆን ካለ የማስወገድ ግዴታ መኖሩን ኦሕን ኢአ ከልብ ያረጋግጣል፣

ማንም ግለሰብ ወይም የአመራር አካል ያለመንግሥት ፈቃድ ከውጭ አገር ዜጋ መነጋገር ወይም መወያየት አይፈቀድለትም፤ ኢድርጎ የተገኘ በአገር ክሕደርት ወንጀል መከሰስ እንዳለበት ኦ ሕ ን ኢ አ ያምናል፤

❖ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ለዘመናት ተዋድቀው ባቆዩዋት ሀገራቸው ሕዝባችን እንደባህተዋር በመታየት ከመሬት ባለበትነት የተገለሉ እንዳይሆኑ ለጎጆ መቀለሻም ሆነ ለመተዳደርያ የግል መሬት ሊኖራቸው እንደሚገባቸው ኦ ሕ ን ኢ አ በጽኑ ያምናል፣

አንድ የውጭ አገር ዜጋ ኢትዮጵዊን ከስሶ ከፍርድ በት ሊያንገላታው እንደማይችል ኦሕን ኢአ በጽኑ ያምናል፣

❖ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ መብቱ በኢትዮጵያ መንግሥት መከበር እንደሚኖርበትያም በጽኑ ያምናል፣ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ በደል ቢፈጸምበት ጉዳዩን መከታተልና የዜጋውን መብት የማስጠብቅ ኃላፊነት እንዳለበት የኦ ሕ ን ኢ አ ያምናል

- ወደ ለላ አገር የሸሸውን የፖለቲካ ሰው ማሳደድና ማጥቃትን ኦሕን ኢአ አበክሮ ሲያወግዝ በሕዝብ ላይ ኣደጋ ኣድርሶ የኮበለለውን ግን ቢቻል ወደ ኣገር አስመጥቶ አምጥበነጻ ፍርድ በት ካልተቻለ ባለበት አገር ፍርድ በት መዳኘት እንዳለበት በአጽኖት ያሳስባል፣
- አንዳንድ ግለሰቦች በፖለቲካ ስም ልዩ ጥቅማጥቅም ለማግኘት የሚሯሯጡትን ኦ ጽ ን ኢ አ ያወግዛል ሤራውንም ወደ ሕዝብ ያጋልጣል

ሕዝባችን የአገራችንን ሉኣላዊነት የማይጎዳ ዉሎችን ከለላ ዘጋ ጋር መቻሉ ቢደገፍም በቅድሚያ ለአገር ደህንነት ቢሮ ማሳወቅና አዎትዊ ምላሽ ምግኘት ይኖርበታል፤

ወጣቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአገሪቱ ፖለቲካዊ እንቅስቃሰ ውስጥ በንቃት መሳተፍ እንዳለበት ኦሕን ኢአ ያምናል፤

ወጣቱ ትውልድ ስለአገር ታሪክ የግድ ማወቅ የሚስፈልገው ነገ ተረካቢ ስለሆነ ከሱሰኝነት ነጻ መሆን እንዳለበት ኦሕን ኢአ ያምናል ፣ለተግባራዊነቱም ቁጥጥር ያደርጋል፤

ወጣቱ በመንግሥታዊ የሥራ እንቅስቃሰ ም መሳትፍ እንዳለበት ኦሕን ኢአ ያምናል፤

ክፍል ሁለት

ምጣነ ሐብት

- ኦ ሕ ን ኢ አ ከሠርቶ ኣደሩ ሕዝባችን በመግባባት የአገራችን ምጣነ ሐብት እንዲያድግ የሚፈልግበት ድጋፍ ያደርጋል፣
- ለአገርችን ምጣነ ሐብት ዋልታ የሆነው የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ኦ ሕ ን ኢ አ ጥረት ያደርጋል.
- ኢትዮጵያውያን በሙያቸው መስከተሰማርተው ያገራቸውን ምጣነ ሐብት ማሳደግ እንዳለባቸው ኦሕን ኢአ ያምናል፣ አስፈላጊዉን ድጋፍም ያደርጋል፣
- የአገራችን የከርሰ ምድር ሐብት፡በመንግሥት፡እጅ፡እንዲሆን፡ኦሕንኢአ ያምናል፣
- የአገራችን ምጣነ ሐብት እድገት አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ ለቱሪስት መስህብ ለሚያገለግሉ ቦታዎች፣ ቁሶች ወዘተ መንግሥት ጥበቃ እንዲያደርግላቸው ኦሕን ኢአ ያሳስባል፣
- የአገራችን ደን እየተመናመነ ስለሆን ዘጎች ዛፍ እንዲተክሉ ኦሕን ኢአ የበኩሉን ጥረት ሲያደግ ምርጥ ዛፎች እንደአየሩ መተከል ያለባቸው ለተካዩ አካል እንዲቀርብ ያደጋል
- ዘጎች ከሚያገኙትገቢ የሚከፍሉት ግብር በአግባቡ መዋላቸውን መንግሥት ማሳወቅ እንደምኖርበት ኦሕን ኢአ ያምናል፣ ይቆጣተራልም፣
- ኢትዮጵያውያውያን እየተራቡ አህልና የእንስሳት ተዋጽኦ ለውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ተብሎ መሸጥ እንደለለበት ኦሕንኢአ አበክሮ ያሳስባል
- ለዛረ የአገራችን ምጣነ ሓብት መንኮታኮትና ማዘቅዘቅ ምክንያቱ የወያነ የመረት ቅርምት ፖሊሲ ስለሆን ይህ ፖሊሲ ከወያነ አስተዳደር ጋር መደምሰስ እንዳለበት ኦሕን ኢአ የምናል ለከባቢ አየር ጥበቃ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፤
- ሠራተኛው ሕዝባችን ለአገር ምጣነ ሐብት እድገት ወሳኝ ስለሆነ መንግሥት ልዩ እንክብካበ እንዲያደርግለት ኦሕን ኢአ ያሳስባል፤
- ለሠራተኛው ሕዝብ ሞራል መጠበቂያ የሚሆን እንደሁኑታው የገንዘብ ድጎማ እንዲደረለት ኦሕንኢአ ያሳስባል፤

መንግሥትና ኦሕንኒአ በመተባበር በመቀነስ በጋራ ምሥራት እንዳለባቸው ያምናል፤ ሥራ አጥነትን ለማስወገድ ከአገር ዉስጥና ከውጭ አገር ከሚገኙት ምሁራን ጋር በመነጋገር መፍትሃ እንደሚገኝ ስለሚያምን አብሮ መሥራት ጠቀመታ እንዳለው ያምናል፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚልኩት ገንዘብ በአግባቡ በሥራ ላይ መንግሥት ለምሁራን መግለጽ እንዳለበት ኦሕን ኢአ በጽኑ ያምናል

- ለሕንፃ ሥራና ለለላም ተብሎ የሚቆረጡ ዛፎች ለአየር መዛባትና ለምጣነ ሐብት መዳከም አስተዋጾ ስለሚያደርገው መከልከል ሲኖርበት በምትኩ ብረት መጠቀም እንዳለበት ኦሕን ኢአ አማራጭ ያቀርባል
- የአገርን እድገት የሚያቀ ጭጩ ጉቦ .መደለያ አራጣ ማበደር ቁማር ኮንትሮባንድ ወዘተ ስለሆኑ ኦሕን ኢአ በጽኑ ያወግዛል እርምኝ እንዲወሰድም ይጥራል
- ዘጎች የአገሪቱን ምጣነ ሐብት እድገት ከሚያገኙት ገቢ ለመንግሥት ግብር የመክፈል ግደታ እንዳለባቸው በጽኑ ያምናል
- መንግሥት የቁጠባ አሠራር በሕዝብ ውስጥ ሥርስሮ እንዲገባ ኅብረተሰቡን ማስተማር እንዳለበት ኦሕን ኢአ አበክሮ ያሳስባል፣ በተለይ ወጣቱ ነገ የአገር ተቀባይ ስለሆነ ስለቁጠባ ስልት ከወዲሁ መማር እንዳለበት ኦሕን ኢአ ያምናል፣

ክፍል ሦስት

<u>ወታደራዊ መርሆ</u>

- <u>የኦሮሞ ሕዝብ ኢትዮጵያን በመከላከሉ ረገድ ከለሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመተባበር አጥር ሆኖ የኖረ ሲሆን ዛረ አፍራሽ ወያነን ጠራርጎ ለማጥፋት በሚደረገው ትንቅንቅ ግንባር ቀደም ተሰልፊ መሆኑን ኦሕን ኢአ ያረጋግጣል፤</u>
- <u>አገር ሻጭ ወያነን ከኢትዮጵያ ማስወገድ የሚቻለው በአፈሙዝ ብቻ መሆኑን ሲያምን ለአፈሙዝ ትግሉ ማዐከላዊ ወታደራዊ እዝ መኖር እንዳለበት ይምናል</u>
- <u>ማዐከላዊ አመራር ከለለ ግን ትግሉ ግቡን ለመምታት ከባድ መሆኑን ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያስከፍል ኦሕን ኢአ ስለሚያምን ትግሉን ከመረት ላይ መጀመርን መርጦ እነሆ አንዳንድ ቁምነገሮችን እያሳየ ነው፤</u>
- <u>ኦሕንኢአ ወያኔን ከአንድነቱ ኋይሎች ትብብ ከፈነገለውበኋላ በአገር አንድነት የሚያኑ ተሰባስበው የሽግግር መንግሥት አንድመርቱ ሀሳብ ያቀርባል አስከዚያ አገር ያለመሪ መኖር ስለማትች ከድርጅቶች መከከል በዲሞክራሲያዊ</u> አሠራር አንድመርጥ ሥያደርግ ራሱም አብሮ ይመርጠል ሊመረጥም ይችላል
- ኦሕን ኢአ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች ተባብረው እንዲሠሩ ያበረታታቸዋል በዚህ አኳያ በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሚታየው ሰላማዊ ፉክክር ለአገር እንደሚጠቅም ሁሉም እንዲያውቁ የበኩሉን አስተዋጾ ሲያደርግ በአገር መከላከሉ ረገድ ሁሉም እንዲተባበር ጥሪ ያቀርባል፣
- አገር አፍራሽ የበተነው የቀድሞ የኢትዮጵያ በሕይወትና የአካል ብቃት ያላቸው ፈቃደኛ የሆኑ ሠራዊቱን በዘመናዊ መልኩ እንዲያሠለጥኑ ኦሕን ኢአ አገራዊ ጥሪ ያቀርባል፤
- የአገሪቱን ንግድ በተመለከተ ማዕከላዊ የገበያ አሠራር መሆን እንዳለበት ኦሕን ኢአ ያምናል፥
- ጥቁር ገባያ አሠራር እንዳይከሰት እንዲሁም የገንዘብ ዝውውር በአግባብ እንዲሠራ መንግሥት እንዲቆጣጠር ጥቆማ ይሰጣል፣

- ከውጭ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡት በማንኛውም ገቢላይ መንግሥት ጠበቅ ያለ ቁጥጥር እንዲያደርግ ኦሕንኢአ ለመንግሥት ጥቆማ ይሰጣል፣
- ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ የከርሰ ምድር ማዕድኖች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆን እንዳለባቸው ኦሕን ኢአ ያምናል፣

- ኢትዮጵያ ሰላም በማስከርበሩ መስከ ለዓለም ብዙ አስተዊጽኦ ሲያደርግ እንደኖረ ታሪከ ይመሰክራል፣ ሠራዊታችን በየሄደበት ቦታ ደሙን አፍስሶ ሕይወቱን ሲገብር ከጥቂት አገሮች በስተቀር ምስጋና አልተሰጠዉም፣

- የዓለም አቅፍ ግዳጅ ለሠራዊአችን ከተሰጠ ከአንድ ሻለቃ ጦር በላይ መላከ እንደልለበት ሲገልጽ ለዚህም ምክር በቱ የወሰነ እንደሆነ ብብቻ መሆን እንዳለበት ያምናል፣ በግዳጁ ላይም የወሰነ ጊዜመጠቆም እንዳለበት የኦሕን ኢአ አበክሮ ያሳስባል፣

- *በአፍርሽ ወያነ ያለምንም ካሳ ለተበተነው የኢትዮጵያ ሠራዊት ካሳ እንዲከፈል ለሚመሠረተው የኢትዮጵያ መንግሥት ያሳስባል፣ ዛረም ጸረ ወያነ በሚደረገው ትግል እንዲሳተፉ በሚስጥር ኦሕን ኢአ ጥሪ ሊያቀርብላቸው ይችላል*

- *ዛረ ሕዝባችንን በመግደል አገራችንን በማፍረስ ላይ ያለውን የወያነን ሠራዊት በወንጀል የሚፈለጉትን ጦር ፍርድ በት እንዲቀርቡ ሲደረግ ከወንጀል ነጻ የሆኑና እድመያቸው ለጡረታ ያልደረሱ ከሚመሠረትው ሠራዊት ጋር ትምህርት ወስደው ሊቀላቀሉ ይችላሉ፥ ለመቀላቀል የማይፈልጉ ደግሞ አገሪቷ ቀደም እንድነበረች አስረክበው በለላ የሥራ ቦታ ተሰማርተው ማገልገል እንደሚችሉ ኦሕንኢአ ያምናል፤*
- *የኢትዮጵያን አንጡራ ሐብት መዝብረው በዘመድ አዝማድ ስም ባገር ውስጥ ወይም ከለላ አገር የሸሸጉ ወይም ሕንጻ የገነቡ በሕይወት ካሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ሲደረግ በሕይወት ከለሉ ዘመዶቻቸው እንዲጠየቁ ኦሕን ኢአ በጥብቅ ያሳስባል፣*
- *በወያነ አስተዳደር ጊዘ የአከባቢ ታጣቂ ሆነው ሲሠሩ የነበሩ ከበደል ነጻ የሆኑ ትምህርት ተሰጥተውቸው ወደ ሕዝብ እንዲቀላቀሉ ይደርጋል ዳግም የጦር መሣሪያ እንደማይሰጣቸው ኦሕን ኢአ ያምናል፤*
- *ዉትድርና ሙያ ስለሆነ ለዓመታት ገደብ ማንም ሰዉ ማገልገል እንደለለበት ኦሕን ኢአ ያረጋግጣል፤ ይህ ስንኝ ብሐራዊ ዉትድርናን አይመለከትም፤*

*ክፍል አራት*
*ማኅበራዊ ግንባታ መርሆ*

- *በዚህ ርእስ ሥር ኦሕንኢአ የኦሮሞ ሕዝብን ማኅበራዊ እንደት መከናወን እንዳለበት ይጠቁማል፤*
- *ጉዳይ ወያነዎች የሚዳኙበት ሕግና ዳኞች ለመመልመል ከለሎች የኢትዮጵያ ድርጅቶች ጋር ይመክራል፣*
- *ወያነ በግፍ ያሰራቸው ከእሥር በት እንዲለቀቁ ኮሚተ አዋቅሮ ሥራውን በአስቸኳይ ያስጀምራል፣*
- *ኦሕን ኢአ ለሥራው መቃናት በመጀመሪያ ወጣቶችን ያደራጃል፣*
- *የኦሮሞ ወጣቶች የቀለም ትምህርት ስምንተኛ ክፍል የማጠናቀቅ ግደታ እንዳለባቸው ኦሕን ኢአ አበክሮ ያስገነዝባል፤*
- *ኦሕን ኢአ በከፍተኛ የሙያ ትምህርት በቶች የሚማሩ ያለ ምንም ክፍያ መማር እንዳለባቸው ያምናል፣*
- *ለኦሮሞ አርብቶ አደርና አርሦ አደር አጫጭር ሙያ ነክ ኮርሶች በየጊዘው ማግኘት እንዳለባቸው ኦሕን ኢአ ያምናል፣*
- *በወያነ አፍራሽ አስተዳደር በሕዝባችን ላይ የተንሰራፉ ጎጂ ባህሎች እንዲወገዱ ከፍትኛ ጥረት ያደርጋል፣*

ለኦሮሞ አርሦ አደርና አርብቶ አደር ሕዝባችን መንግሥት ለሙያው የሚያገለግል የትክኖሎጂ ውጠቶችን ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገባላቸው ኦሕን ያሳስባል፣

ትዳር ክቡርና ሆኖ ሳለ በአለመግባባት መፋታት ከተፈለገ በጋራ ያፈሩትን ንብረቶች እኩል ሲካፈሉ ከሚካፈሉት ለመንግስት ቀረጥ የመክፈል ግደታ እንዳለባቸው ኦሕኒአ ያምናል፤

- *ሥራ ፈላጊዎች በሥራ ላይ እንዲሠማሩ ጉዳዩን የሚከታተሉ ኮሚተ አዋቅሮ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፥ በወያነ ሠራ በአግራችን ምጣነ ሐብት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከመድረሱ ለላ ብዙ ፋብሪካዎች ወድመዋልም ፈርሰዋልም ስለሆነም የፈረሱ ፋብሪካዎች እንዲጠገኑ ከባለሀብቱ ጋር ይመክራል፣*
- *አርብቶ አደሩ የእንስሳቱን ጭራ ተከትሎ ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ወደ ቦታ ከመንከራተት በአንድ በተወሰነ አከባቢ ከትመው መንግሥት እገዛ እንዲያደርግ ኦሕን ኢአ ጥቆማ ይሰጣል፣ ለአፈጻጸሙም እገዛ ያደርጋል፤*
- *በየቦታው ተበታትኖ የሚኖረውን የኦሮሞ ሕዝባችን ወደ አንድ ማእከል ማሰባሰብና ማደራጀራጀ አስፈላጊ ኦሕን ኢአ ለመንግሥት ጥቆማ ይሰጣል፤*
- *በኦሮሞ መረትም ሆነ በአጎራባች ሕዝቦች ክልል የጠና ተቋሞች እንዲስፋፉ ኦሕን ኢአ ያበረታታል፣*

- የወያኒ ጉዳይ የትምህርት መርሃ ግብር ተወግዶ ዓለም አቀፍ የትምህርት ፖሊሲ በአገራችን እንዲተገበር ኦሕን ኢአ በጥብቅ ያሳስባል፣
- በመምህራንና በተማሪዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በአግባቡ መሆን እንዳለበት ኦሕንኢአ ሲያሳስብ መምህራን በማስተማሩ ረገድ ሙሉ ነጻነት እንደሚኖራቸውና ማንም አካል ሊሰገድድ አይችልም፣ ፈተናንም በተመለከተ መምህራን ከማንም ተፅ ዕኖ ውጭ መሆን እንዳለባቸው ኦሕን ኢአ ያምናል፣
- የአገሪቱ ታሪካዊ ቅርሶች በመንግሥት እንዲጠበቁ ኦሕን ኢአ ጥቆማ ያቀርባል፣ ገዳማትና በታሪካዊ ቅርስነት የሚታወቁ ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ኦሕን ኢአ ለመንግሥት ጥቆማ ይሰጣል፣
- የአገር ጎብኚዎች ለአገራችን ምጣነ ሀብታዊ መጎልበት ከፍተኛ ጠቀመታ ስላአላቸው ሆተሎችና በቂ የመዝናኛ ቦታዎች በጥሩ ሁኔታ እንዲያዙ ኦሕን ኢአ ያሳስባል፣
- ጎታች ባህሎች መወገድ እንዳለባቸው ኦሕን ኢአ ያምናል፣
- ወጣቱ ትውልድ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኛ እንዳይሆን ኦሕን ኢአ ከፍተኛ ክትትል ያደርጋል፣ እርምጃም ይወሰዳል፣ ያለ እድሜ ገደብ የሚከናወኑ ድርጊቶች እንደጫት መቃም፣ ሺሻ ማጨስ፣ ሲጋራ ማጨስ አልኮሆል መጠጣት፣ ወዘተ ኦሕን ኢአ ያምናል.
- ሱቅ በደረተዎች፣ ጉልት ነጋደዎች ጥቃቅን ሸቀጥ አዟሪዎች ወዘተ የመንግስት ግብር መጠየቅ እንደለለባቸዎሕን ኢአ ያምናል፤
- ባሕላዊ መድኃኒቶች በሐኪሞች ተመምርረው በሥራ ላይ ቢውሉ ኦሕን ኢአ አሠሩን ይደግፋል፣
- ሰውሠራሽ ወይም የተፈጥሮ አደጋ በአንድ በአገሪቱ ቦታ ቢከሰት የኦሕን ኢአ አባሎች አስተዋጻኦ ያደርጋሉ. ነፃ ጉልበትም ያበረክታሉ፣
- በገጠሪቱ ኦሮሞ ክልል ሥራ አጥነት እንዳይስፋፋ ሠፋፊ የመንግሥት እርሻዎች እንዲዘረጉ ኦሕን ኢአ ለመንግሥት አጀንዳ አቅርቦ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፣የአገሪቱ ለም አፈር በጎርፍ እንዳይወሰድ ሁሉ ሰው በአከባቢው የእርከን ሥራ እንድለመድ ያስተምራል፣
- በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅ እንስሳትና ዕፅዊት በስጦታ መልክ ወይም በለላ መልኩ ተላልፈው ኦሕን ኢአ ያጠነቅቃል፣ ድርጊቱ ተፈጽሞ ከተገኘ በአድራጊው ላይ ከፍተኛ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
- የአራሹና የሸማቹ ግንኙነት ግንኙነት እንዲጠናከር ኦሕን ኢአ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፣
- ጥቃቅን ከተማዎች ሣይቀሩ የሕዝብ ሱቆች እንዲከፈቱ ኦሕን ኢአ ጥረት ያደርጋል፣

ይህ መሠረተ ዓላማ እንደአስፈላጊነቱ በአባላቱ ጠቅላላ ጉባዔ ታይቶ የሚጨመር ወይም የሚቀነስ ወይም የሚሻሻል ካለ ኦሕን ኢአ ሙሉ ለሙሉ እንደሚቀበል በትሕትና ይገልፃል፤

**አንድነታችን ለዘለዓለም ፀንቶ ይኖራል**